# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)
# *Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)*

(አንድነት/United)

ግንቦት ፳፩ ቀን ፪ ሺህ ፱ ዓ. ም
May 29, 2017

## <u>ኮሎኔል አስናቀ እንግዳ የአርበኛም አርበኛ ነበሩ</u>

ኮሎኔል አስናቀ እንግዳ በዚህ ዓለም የኖሩባቸውን አንድ ምዕተ-ዓለም ዓመታት፤ የጀግናና የአርበኛ ኑሮና ትግል አድርገዋቸው በቅርቡ ሕይወታቸው አልፏል። ጀግናው ኮሎኔል የአርበኝነትና የአገር ፍቅር የሚንያንገበግባቸው አገር ወዳድ ብቻ ሳይሆኑ፤ ብዕራቸውም እንደወኔያቸው እሳት የሚተፉ ነበር። ለተለያዩ ጋዘጦችና መጽሄቶች በአገር ጉዳይና በታሪክ ዙሪያ ጽሁፎችን ላለፉት 50 ዓመታት ከማበርከታቸው በላይ፤ ዝነኛ የመጽሐፍ ደራሲም ነበሩ። ከጻፏቸው መጻሕፍት መካከል "ዐረባዊ አፄነትና የአፍሪካ ቀንድ ፍዳ" የሚልና "ሽክም የማይከብደው ሕዝብ" የሚሉ ይገኙባቸዋል።

ኮሎኔል አስናቀ እንግዳ በንጉሡ ዘመን "መንግሥት ልትገለብጥ አሲረሃል" ተብለው ሁለት ጊዜ ለእስር ሲዳረጉና ደመወዛቸውም ሲቋረጥ፤ ልጆቻችው ከስድስት ወር ሕፃን እስከ 14 ዓመት ዕድሜ ክልል ውስጥ ነበሩ። ባለቤታቸው ወይዘሮ አበባ ንጉሤ በፅናትና በቆራጥነት የጀግና ልጆችን በሚገባ ተንከባክበው አሳድገዋል። ለዚህም ባለቤታቸው ኮሎኔል አስናቀ ውለታቸውን በመጽሐፋቸው ዘክረዋል።

ከመጽሐፋቸው ትዝታ፣ በ1957 ዓ. ም ከአንድ ወዳጃቸው ጋር በጂፕ መኪና ከሐረር ወደ ድሬዳዋ ሲሄዱ፤ ንጉሡ ወደ ድሬዳዋ እንደሚመጡ በማወቅ ለወዳጃቸው ያሉትን ያስታውሳሉ። "በግፋዊ አስተዳደር ውስጥ በመኖርና አለመኖር መካከል ልዩነት የለውም። በአድኂዊ ሥርዓት ታፍኖ ከመኖር አለመኖር ይመረጣል" ብለዋል። ይህን ያሉት በንጉሡ ላይ እርምጃ ቢወሰድ፤ ጣጣው ለልጆቻቸው እንደሚተርፍ ወዳጃቸው ላነሳላቸው አስተያየት ምላሽ ነበር።

**P.O.Box 91384** **Phone: 202- 241 2078**
**Los Angeles, CA 90009** **eprp_united@eprp-ihapa.com**

ንጉሡን የተካው የደርግ አስተዳደርም ለኮሎኔል አስናቀ የህሊና ዕረፍት አልሰጣቸውም፤ አልተመቻቸውም። በብልሹ አስተዳደሩና በጨፍጫፊነቱ በመማረር በታጋይነት ገጠር ገብተዋል። በገጠሩ ቆይታቸውም በተለያዩ ግዛቶች ውስጥ በመንቀሳቀስ ባላገሩንና ባላባቱን በማሰባሰብ አገር ወዳድ ድርጅት እንዲመሠረት ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል።

ብልሹው የደርግ አስተዳደር የጀግናውን ዝና ለማጠልሸት በራሪ ወረቀቶችን በገጠር በአውሮፕላን እስከመበተን ደርሶ ነበር። ጀግናው ግን በዚህና በመሳሰሉት ወራዳ ተግባራት ሳይበገሩ ትግላቸውን ለዓመታት አካሂደዋል።

ህወሓት/ኢህአዴግ ሥልጣን ሲይዝም፤ እነሆ ለሦስተኛው አምባገነናዊ አገዛዝም አልተንበረከኩም። እንዲያውም የጎሣ-ተኮር አካሄድ ሊያመጣ የሚችለውን አደጋ በነቢይነት አስቀድመው ካመላከቱት አረጋውያን ግምባር ቀደም ናቸው።

ኮሎኔል አስናቀ ለፓርቲያችን ጥሩ ወዳጅ ነበሩ። የኢሕአፓን ፅናትና አይበገሬነት አድናቂ ነበሩ።

ዘመን ተሻጋሪ ትግላቸው የተመኙለትንና የታገሉለትን የሕግ የበላይነትና ዴሞክራሲያዊ አስተዳደር በኢትዮጵያ ሳያዩ ሕይወታቸው በማለፉ ኢሕአፓ (አንድነት) እንደ ታጋይ ዜጋ ይቆጨዋል። ይሁን እንጂ ፓርቲያችን እኚህ አርበኛ ለወጣቱ ትውልድ ትተውለት ባለፉት የትግል አሻራና ፅናት ይጽናናል። አዲሱ ትውልድም አረጋዊው የደከሙበትን ትግል ከግብ እንደሚያደርስ ፓርቲያችን ዕምነቱ ፅኑ ነው።

ኢሕአፓ (አንድነት) በኮሎኔል አስናቀ እንግዳ ከዚህ ዓለም በሞት መለየት የተሰማውን መሪር ሃዘኑን እየገለጠ፣ ቤተሰቦቻቸውና ወዳጆቻቸው እንዲጽናኑ ልባዊ ምኞቱን ይገልጻል።

**P.O.Box 91384** **Phone: 202- 241 2078**
**Los Angeles, CA 90009** **eprp_united@eprp-ihapa.com**